የግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረጀብ 3/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚንስተር ፌብሯሪ 4/2022 ግ.

# የተከበሩት ወራት የሰብአዊ ሰላም መልእክት ናቸው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ إِنَّ عِدَّةَ الشُّهُورِ عِنْدَ اللَّهِ اثْنَا عَشَرَ شَهْرًا فِي كِتَابِ اللَّهِ يَوْمَ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ مِنْهَا أَرْبَعَةٌ حُرُمٌ ذَلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡

(የወሮች ቁጥር አላህ ዘንድ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት ቀን ዐሥራ ሁለት ወር ነው፡፡ ከእነሱ አራቱ የተከበሩ ናቸው፡፡)

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል፡

አላህ (ዐ.ወ.) ለባሮቹ ከቸረው ትሩፋት አንዱ በነሱ በጎ ሥራዎች አጥፍ ድርብ የሚሚያደርግባቸውና ኃጢያታቸውንም በምህረት የሚያልፍባቸው የደግና የበረከት ወራት የመረጠላቸው መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَذَكِّرْهُمْ بِأَيَّامِ اللَّهِ}

(የአላህንም ቀኖች አስገንዝባቸው)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ጌታችሁ «ዐ.ወ.» በዘመናችሁ ቀናት ትሩፋቶች የሚያወርድባቸው ጊዚያቶች አሉት፡፡ በመሆኑም እነሱን አላማ አድርጓቸው፡፡ ምናልባትም አንዳችሁ አንድ ትሩፋት ያጋጥመውና ከዚያ በኋላ ምንጊዜም መንዳካነት አያገኘው ይሆናልና)፡፡

ከነዚህ የእምነት ወራት መካከል የተከበሩት ወራት ይካተታሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ስለነሱ አጠቃላይ ምንነት አንድህ ይላል፡

{إِنَّ عِدَّةَ الشُّهُورِ عِنْدَ اللَّهِ اثْنَا عَشَرَ شَهْرًا فِي كِتَابِ اللَّهِ يَوْمَ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ مِنْهَا أَرْبَعَةٌ حُرُمٌ ذَلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ فَلَا تَظْلِمُوا فِيهِنَّ أَنْفُسَكُمْ}

(የወሮች ቁጥር አላህ ዘንድ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት ቀን ዐሥራ ሁለት ወር ነው፡፡ ከእነሱ አራቱ የተከበሩ ናቸው፡፡ ይህ ቀጥተኛው ሃይማኖት ነው፡፡ በእነርሱ ውስጥም ነፍሶቻችሁን አትበድሉ፡፡)

ይህን ጉዳይ ነብያችን በስንብት ድስኩራቸው እንድህ በማት አብራርተውታል፡ (እነሆ ዘመኑ አላህ ሰማያትና ምድርን በፈጠረ እለት አንዳስቀመጠው እንደገና ተመልሷል፡፡ ዓመት አሥራ ሁለት ወራት ነው፡፡ ከነሱም አራቱ ወራት የተከበሩ ሲሆኑ ሦስቱ ተከታታይ ዙልቃዕዳ፣ ዙልሒጃ፣ ሙሐረምና ከጁማዳና ከሸዕባን መካከል ያለው የሙደር ረጀብ ናቸው)፡፡

የተከበሩት ወራት ከአላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ ክብር፣ ከፍተኛ ቦታና ቅድስና አላቸው፡፡ የተከበሩ የሚል ስያሜ የተሰጣቸውም ያላቸው ክብር ታላቅ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የእስልምና እምነት ህግጋት በነሱ ግድያና ክብር ማርከስ አርም መሆናቸውን በጥብቅ አረጋግጠዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَسْأَلُونَكَ عَنِ الشَّهْرِ الْحَرَامِ قِتَالٍ فِيهِ قُلْ قِتَالٌ فِيهِ كَبِيرٌ}

(ከተከበረው ወር (ከረጀብ) በርሱ ውስጥ ከመጋደል ይጠይቁሃል፡፡ በላቸው «በርሱ ውስጥ መጋደል ታላቅ (ኀጢአት) ነው፡፡)

የተከበሩት ወራት ለሰው ልጅ በሙሉ የሰላም መልእክት አዝለዋል፡፡ ሰላም ደግሞ ከታላቁ አላህ መልካም ስሞች አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ}

(እርሱ አላህ ነው፡፡ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ፣) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የእዝነትና የሰላም መልእክተኛ መሆናቸውን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጾታል፡

{وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَالَمِينَ}

(ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከስግደታቸው ሁሉ በኋላ እንድህ በማለት አላህን ያወድሱ ነበር፡

(اللَّهُمَّ أَنْتَ السَّلَامُ وَمِنْكَ السَّلَامُ تَبَارَكْتَ يَا ذَا الْجَلَالِ وَالإِكْرَامِ).

የእስልምና እምት ለግድያ ወይም ደምን ለማፍሰስ የሚቻኮል ሃማኖት አይደለም፡፡ ይልቁንም ግድያና ደም ማፍሰስን በማንኛውም መንገድ ይከላከላል፡፡ ወደሰላም ያዘነበላልና እሱንም ያሚያረጋግጥ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ በማለት ግለጾታል፡

{وَإِنْ جَنَحُوا لِلسَّلْمِ فَاجْنَحْ لَهَا وَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ إِنَّهُ هُوَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ}

(ወደ ዕርቅም ቢያዘነብሉ ወደ እርሷ አዘንብል፡፡ በአላህም ላይ ተጠጋ፡፡ እነሆ እርሱ ሰሚ ዐዋቂ ነውና፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ጠላት ጋር መገናኘትን አትመኙ፡፡ ከአላህም ደህንነትን ለምኑ፡፡ ነገር ግን ከተገናኛችሁ ታገሱ)፡፡ የእስልምና እምነት መልእክት

ሰላምና መስማማት ሲሆን አላማው ደግሞ በመላው ሰው ልጅ ዘንድ ደስታን ማስፈን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أتقاكم إن الله عليم خبير}.

(እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡)

*****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡
የተከበሩ ወራትን ማላቅ በነሱ ውስጥ ከማንኛውም የሸብርና የጸንፈኝነት ተግባር መታቀብን የሰላማዊያንን ደም ከማፍሰስና እነሱን ከማስጨነቅ መራቅን ያካትታል፡፡ እንድሁም በነዚህ ወራት ኢባዳዎችን በማብዛት ወደአላህ (ዐ.ወ.) ለመቃረብ መጣርንም ያጠቃልላል፡፡
በመሆኑም በኢባዳ ተጋድሎ በማድረግ፣ ለፈጣሪ በመታዘዝና ወደሱም በመቃረብ መንፈሳችንን በማጽዳት እነዚህን ወራት ማክበርና ማዋብ ይጠበቅብናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَافْعَلُوا الْخَيْرَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

(በጎንም ነገር ሥሩ፣ ልትድኑ ይከጀልላችኋልና፡፡)

ነብያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከተከበሩት ወራት ጹም፡፡ እንድሁም ጾምን ተው፡፡ ከተከበሩት ወራት ጹም፡፡ እንድሁም ጾምን ተው፡፡ ከተከበሩት ወራት ጹም፡፡ እንድሁም ጾምን ተው)፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ከነዚህ ወራት አንዱ የረጀብ ወር ነው፡፡ ቃሉ ተርጂብ

ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉምም ማክበር ማለት ነው፡፡ የጥንት አረቦች በሱ የጦር ድምጽ ስለማይሰማበት ደንቆሮ የሚል ስያሜ ሰጥተውት እንደነበር ይህገራል፡፡ ይህ ወር በሱ የነብየችን (ሶ.ዐ.ወ.) የኢስራእና ሚዕራጅ ታምራት የተስተናገዱበት ወር ነው፡፡ እሱም የደግ ነገሮችና የበረከት ወር ነው፡፡ አቡከር አልወራቅ አልበልኺይ የተባሉት ሊቅ « ረጀብ የአዝመራ መዝሪያ ወር ነው፡፡ ሸዕባን ደግሞ አትክልቱ ውሃ የሚጠጣበት ወር ነው፡፡ ረመዳን ደግሞ አዝመራው የሚታጨድበት ወር ነው» ይሉ ነበር፡፡

የተከበሩ ወራት ያዘሉትን መልካም አጋጣሚ ለአላህ (ዐ.ወ.) በመገዛት ምድርን በማልማት፣ ሥራን በጥራት በማከናውን፣ በጎ ሥራን በማብዛት፣ ምግብን በመለገስ፣ የመተጋገዝና የመተዛዘን መንፈስን በማስፋፋት መጠቀማችን እጅግ ተፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከሰዎች ከአላህ ዘንድ በጣም በላጩ ለሰዎች በጣም ጠቃሚው ነው፡፡ ከሥራዎች አላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ እጅግ በላጩ ከሱ ጭንቅን በማስወገድ ወይም እዳውን በመከፈል ወይም ራሀቡን በማስወገድ በአንድ ሙስሊም መንፈስ ደስታን ማስገባትህ ነው፡፡ እኔ የሱን ጉዳይ ለማውጣት ከወንድሜ ጋር መሄዴ በዚህ መስጊድ -በመድናን መስጊድ ማለታቸው ነው- ወር በኢዕቲካፍ ከመቀመጤ ይበልጥብኛል፡፡ እሱን ማውጣት እያቻለ ቁጭቱን የገታ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን ልቡን በእርካታ ይሞላለታል፡፡ ጉዳዩን እስከሚያወጣ ድረስ ከወንድሙ ጋር የተጓዘ ሰው እግሮች በዳጥ በሚጠመዱበት የትንሳኤ ቀን አላህ እግሮቹን ያጠነክርለታል)፡፡

ጌታችን ሆይ! ረጀብና ሸዕባንን ባርክልን ከረመዳንም አድርሰን፡፡ አሚን፡፡